# የግላዊነት ልምዶች ማስታወቂያ

Notice of Privacy Practices / Amharic



Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

# የግላዊነት ልምዶች የጋራ ማስታወቂያ

## ለ Seattle Children’s ሆስፒታል እና የተወሰኑ ሌሎች አቅራቢዎች

ማስታወቂያው በ 1/10/18 ተግባራዊ ይሆናል

## ማጠቃለያ

በ Seattle Children’s ሆስፒታል ውስጥ እንክብካቤ በሚያገኙበት ጊዜ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ እና ሌሎችም ስለእርስዎ፣ ስለ የጤና ታሪክዎ እና ስለ ህክምናዎ መረጃዎችን ይሰበስባሉ እንዲሁም ይቀበላሉ። ይህ “የታካሚ የጤና መረጃዎ” በመባል ይታወቃል።

አብዛኛዎቹ የ Seattle Children’s ሆስፒታል ታካሚዎች ልጆች ናቸው። በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ስለ “እርስዎ” ወይም “የእርስዎ” ብለን ስንናገር ስለ ታካሚው እየተነጋገርን ነው። ታካሚው ልጅ ይሁን ወይም ጎልማሳ ምንም ችግር የለውም። ስለ “ስለ እርስዎ መረጃ” ስንል የታካሚው፣ የታካሚው የሕግ ተወካይ፣ ወይም ስለ በሽተኛው መረጃ ለመቀበል የተፈቀደለት ሰው መረጃ ይፋ ማድረጉን ማለታችን ነው። የጤና መረጃዎን የመጠበቅ ሀላፊነት አለብን።

እኛ የሚከተለውን ለማድረግ በሕግ ይጠበቅብናል፦

- የመረጃዎን ግላዊነት መጠበቅ።
- ስለ ግላዊነት ልምዶቻችን በተመለከተ ይህንን ማስታወቂያ ማቅረብ።
- በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ የተገለጹትን የግላዊነት ልምዶች መከተል።
- የታካሚ የጤና መረጃዎ ተጥሶ ከሆነ ለእርስዎ ማሳወቅ።

አንዳንድ መብቶች አሉዎት። የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- የታካሚዎን የጤና መረጃ ቅጂዎች መመልከት እና መቀበል ይችላሉ።
- የታካሚዎ የጤና መረጃ በተመለከተ ለውጥ እንዲደረግ ወይም መረጃ እንዲጨመር መጠየቅ ይችላሉ።
- የታካሚዎ የጤና መረጃ ከ Children’s ውጭ የተገለጠበትን ወይም የተጋራባቸውን መንገዶች ዝርዝር እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- እርስዎን በሌላ መንገድ እንድናነጋግርዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- የታካሚዎን የጤና መረጃ አጠቃቀም ላይ ገደብ እንድናደርግ መጠየቅ ይችላሉ።
- የታካሚ የጤና መረጃዎ ግላዊነት በተመለከተ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

በተጨማሪም፡ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

- በሆስፒታል ቆይታዎ ወቅት ለደዋዮች እና ለጎብኚዎች ስምዎን እና የጤና ሁኔታዎን እንዳንሰጥ መጠየቅ ይችላሉ።
- ከቤተሰብ አባላት ጋር መረጃ እንዳናካፍል መጠየቅ ይችላሉ።

የተወሰኑ ህጎችን በመከተል የታካሚዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም እና ልናካፍል እንችላለን፦

- ሕክምናን ለማከናወን፣ የጤና እንክብካቤ ሥራዎችን ለማከናወን ወይም ክፍያ ለማግኘት።
- ሰራተኞችን እና ተማሪዎችን ለማስተማር እና ለማሰልጠን።
- በተቋማት የግምገማ ቦርድ የጸደቀ ምርምር ለማድረግ።
- በሕግ እንደተጠየቀው ወይም እንደፈቀደው ወይም በጽሑፍ የቀረበው ፈቃድዎ ጋር።

ህጉ ለእነዚህ አይነት የታካሚ የጤና መረጃዎች ተጨማሪ ጥበቃ ይሰጣል፦

- በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታ መረጃ (ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ)
- የአደንዛዥ ዕጽ እና የአልኮሆል አለአግባብ መጠቀም በተመለከተ የሕክምና መዛግብት
- የአእምሮ ጤና መዛግብት

## ይህ ማስታወቂያ የህክምና መረጃዎ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና እንዴት እንደሚጋራ እና እንዴት ይህን የመረጃ ተደራሽነት እንደሚያገኙ ይገልጻል። እባክዎን በጥንቃቄ ያንብቡት።

ይህ ማስታወቂያ መብቶችዎን እንዲሁም የታካሚዎን የጤና መረጃ ግላዊነት የመጠበቅ ኃላፊነታችንን ይገልጻል። ለዚህ መረጃ ስለሚሰጡዎት የጥበቃ ሕጎች ይነግርዎታል። የ Children’s የግላዊነት ልምዶች በሁሉም የ Children’s ታካሚዎች ላይ ይተገበራሉ።

ይህ ማስታወቂያ የታካሚ የጤና መረጃዎ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ እና እንዴትና መቼ ሊገለጽ እንደሚችል ያብራራል። እንዲሁም ይህንን ማስታወቂያ እኛ ልንለውጠው እንደምንችል እና ስለ ለውጦቹ እንዴት ማወቅ እንደምችሉ ይነግርዎታል።

## በዚህ ማስታወቂያ የተሸፈኑ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች

Children's ከሌሎች ድርጅቶች እና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እና በሌሎች የጤና እንክብካቤ ስራዎች ይሠራል። ይህ ማስታወቂያ በእነዚህ አቅራቢዎች የታካሚ የጤና መረጃዎን አጠቃቀም እና ይፋነት በተመለከተ መረጃ ይሰጥዎታል፦

- Seattle Children's ሆስፒታል
- Seattle Cancer Care Alliance (የሲያትል የካንሰር እንክብካቤ አሊያንስ)
- የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሐኪሞችን እና ሌሎች የዩኒቨርሲቲ አደረጃጀቶችን ያካተተ UW Medicine
- UW School of Dentistry (UW የጥርስ ህክምና ትምህርት ቤት)
- Children's የዩኒቨርሲቲ የሕክምና ቡድን
- በተጨማሪም ሌሎች አቅራቢዎች በ Children's ተቋማት እንክብካቤን ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን ሲያቀርቡ ይህንን ማስታወቂያ ለመከተል ይስማማሉ።

### Children's

Children's በጋራ የሚሰሩ እና የታካሚ የጤና መረጃን የሚጋሩ ድርጅቶችን ያጠቃልላል። ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ Children's ክሊኒካዊ እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ ለእነዚህ አገልግሎቶች ክፍያ ለማግኘት እና ሌሎች የጋራ የጤና እንክብካቤ ሥራዎችን ለማከናወን መረጃዎን ያጋራሉ። Children's የህክምና ሰራተኞቹን፣ የጤና አጠባበቅ አቅራቢዎችን፣ ሰራተኞችን፣ የኮንትራት ሰራተኞችን፣ ነዋሪዎችን፣ ተማሪዎችን እና በ Children's ተቋማት ፈቃደኛ ሠራተኞችን ያቀፈ ነው። እነዚህ ተቋማት የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- Seattle Children's ሆስፒታል
- Odessa Brown Children's Clinic
- Children's Bellevue Clinic and Surgery Center
- በዋሽንግተን፣ በአላስካ፣ እና በሞንታና የሚገኝ የ Children's ተመላላሽ ታካሚ ክሊኒኮች። የአሁኑን ዝርዝር በ www.seattlechildrens.org/clinics-programs ይመልከቱ
- Children's Autism Center
- Children's Consulting Nurses
- Children's Home Care Services
- Children's Orthotics & Prosthetics
- Children's Prenatal Diagnosis and Treatment Program
- Garfield/NOVA Teen Clinic

## የታካሚዎ የጤና መረጃ መብቶች

የርስዎን የታካሚ የጤና መረጃ የመጠቀምና ይፋ የማድረግ መብት አሎት። የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

### ቅጂዎችን መከለስ እና መቀበል ይችላሉ።

በሕጉ መሠረት ሌሎች አገዳዎች ከሌሉ በስተቀር የጤና መዝገብዎን ቅጅ የመመልከት ወይም የመጠየቅ መብት አለዎት። ጥያቄዎን በጽሑፍ ማቅረብ ያስፈልግዎታል። መዛግብቱን በተመለከተ የወረቀት ቅጅዉን ወይም የኤሌክትሮኒክ ቅጂውን ለመቀበል ከፈለጉ ሊነግሩን ይችላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቅጂ የመቅዳት ክፍያዎች ሊከፍሉ ይችላሉ። በክልልዎ እና በፌዴራል ደንቦች መሠረት በጊዜ ምላሽ የመስጠት መብት አለዎት። ቅጅውን ወደ ሌላ ሰው እንድንልከው መጠየቅ ይችላሉ።

የእርስዎ የታካሚ የጤና መረጃ መብቶች:

- ቅጂዎችን መከለስ እና መቀበል
- መዝገብዎ ላይ ለውጥ ለማድረግ ወይም መረጃ መጨመር መጠየቅ
- መረጃን ይፋ ማውጣት አስመልክቶ ማወቅ
- የተከለከለ አጠቃቀምን መጠየቅ
- ሚስጥራዊ የሆነ ግንኙነቶችን መቀበል
- ቅሬታዎችን ማቅረብ

## በመዝገብዎ ላይ ለውጥ ወይም ተጨማሪ መረጃ እንዲደረግ መጠየቅ።

በመዝገብዎ ውስጥ ያለው መረጃ ትክክል አይደለም ብለው ካሰቡ ወይም አስፈላጊ መረጃ ጠፍቷል ብለው ካመኑ፡ እኛ መረጃዎቻችን እንድናስተካክል ወይንም እንድንጨምር የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህንን ጥያቄ በጽሑፍ ወደ Children's Privacy Office ማቅረብ አለብዎት። ጥያቄዎ ለቀረበው መረጃ የመለወጥ ወይም የመጨመር ጥያቄ ምክንያት መስጠት አለበት። እኛ ጥያቄዎን እንድንሰጥ የግድ አይጠበቅብንም፡ ነገር ግን የጥያቄዎን ቅጂ ወደ መዝገብ ውስጥ እንጨምራለን።

## ስለ ይፋ ማውጣት ይወቁ።

ሕግ እንደሚፈልገው መሰረት Children's ያዘጋጀው የታካሚዎች የጤና መረጃዎን ማሳወቂያ ዝርዝር ለመቀበል መብት አለዎት። ይህ ዝርዝር ከህክምና ከክፍያ ወይም ከጤና እንክብካቤ ስራዎች ወይም ከፈቀዱዋቸው ይፋዊ መግለጫዎች ጋር የተያያዙ መግለጫዎችን አያካትትም። መረጃዎን በተመለከተ በ 12 ወር ጊዜ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረቡት ጥያቄ ከክፍያ ነጻ ነው። በዚያው በ 12 ወራቶች ውስጥ ለሚቀርቡ ማናቸውም ሌሎች ጥያቄዎች የማቀናበሪያ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋሉ። ጥያቄዎን ለ Children's Privacy Office ማቅረብ ይችላሉ።

## የተከለከለ አጠቃቀምን መጠየቅ

ሂሳብ ከመላካችን በፊት ሂሳብዎ ሙሉ በሙሉ ከከፈሉ Children's ስለ አንድ ነገር ወይም አገልግሎት ለኢንሹራንስ ኩባንያዎ እንዳያሳውቅ የመጠየቅ መብት አለዎት። ለበለጠ መረጃ ወደ የንግድ አገልግሎቶችን በ 206-987-5770 ይደውሉ። እንዲሁም ሌሎች የታካሚ የጤና መረጃዎን ሌሎች አጠቃቀሞች እና ይፋ እንዳያደርጉ ለመገደብ በጽሁፍ እኛን የመጠየቅ መብት አለዎት። እነዚህን ጥያቄዎች መስጠት የግድ አይጠበቅብንም፡ ነገር ግን የምንሰጣቸውን ማናቸውም ጥያቄዎች እናከብራለን።

## ሚስጢራዊነቱ የተጠበቀ ግንኙነቶችን ይቀበሉ።

ስለ ጤና ጉዳዮች በተወሰነ መንገድ ወይም በተወሰነ ቦታ እንድንነግርዎ የመጠየቅ መብት አለዎት። ይህንን በጽሑፍ መጠየቅ አለብዎት። ለምሳሌ፡ በሥራ ቦታ ብቻ ወይም በፖስታ ብቻ እንድናነጋግርዎ ሊጠይቁን ይችላሉ። ጥያቄዎ እንዴት ወይም የት እንደሚገኙ ሊነግረን ይገባል። ጥያቄዎትን የምንፈቅድ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

## ቅሬታዎችን ያቅርቡ።

እኛ የእርስዎ የግላዊነት መብት ጥሰናል የሚል ስጋት ካለብዎ ወይም ወደ መዝገብዎ ለመድረስ ባደረግነው ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ፡ ወደ Children's Privacy Office ቅሬታ ማስገባት ይችላሉ። የግላዊነት ቅሬታ ስላቀረቡ Children's አይበቀልም።

# የታካሚ የጤና መረጃዎ እንዴት እንደምንጠቀምበት

ይህ ማስታወቂያ በ Children's አቅራቢዎች የተፈጠረ ወይም የተቀበለውን የታካሚ የጤና መረጃ ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ይህ እርስዎን ለመለየት እና ያለፈውን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊቱን አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ሁኔታዎን ይዛመዳል። እንዲሁም ከተቀበሉት እንክብካቤ ጋር፡ እና ካለፈው፣ ከአሁን ወይም ለወደፊቱ ከሚከፈለው የእንክብካቤ ክፍያ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ መረጃ ብዙውን ጊዜ በጤና መዝገብዎ ውስጥ ይገኛል። የታካሚ የጤና መረጃዎ የምንጠቀምባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች፦

- እንክብካቤዎን ከሚረዱ የጤና ባለሙያዎች ጋር ለመነጋገር።
- ለሚያገኙት እንክብካቤ ህጋዊ መዝገብ ማቅረብ።
- ለሚቀበሉት እንክብካቤ ክፍያ እንድናገኝ ሂሳቦችን መላክ።
- እርስዎ ወይም የሶስተኛ ወገን ከፋይ ሂሳብዎ ከተቀበሏቸው አገልግሎቶች ጋር የሚዛመድ መሆኑን ማረጋገጥ።

በተጨማሪም Children's ለሚከተሉት ጉዳዮች መረጃ ሊሰጥ ይችላል፦

- የጤና ባለሙያዎችን ለማስተማር።
- የህዝብ ጤና ክንዉኖችን ለመደገፍ።
- የምንሰጠውን እንክብካቤ እና የምናገኘውን ውጤት ለመከታተል፣ ለመለካት እና ለማሻሻል።
- የሕክምና ምርምር መረጃ ለማቅረብ።
- ለድርጅቱ እቅድ ማውጣት።

መዝገብዎን እና የታካሚ የጤና መረጃዎ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ መገንዘብ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይረዳዎታል፦

- መዝገቡ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ።
- ሌሎች የታካሚ የጤና መረጃውን ማንን፣ ምን፣ መቼ፣ የት እና ለምን ሊደርሱበት እንደሚችሉ ለማወቅ።
- መረጃን ለሌሎች ለማጋራት ፈቃድ ሲሰጡ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ማድረግ።

## ያለ እርስዎ ፈቃድ መረጃዎን እንዴት እንደምንጠቀምበት እና እንዴት እንደምንገልጠው

ያለ እርስዎ ፈቃድ የታካሚ የጤና መረጃዎን እንዴት ልንጠቀምበት እና ልናካፍል የምንችልባቸው አንዳንድ ምሳሌዎች እነሆ፦

ያለ እርስዎ ፈቃድ መረጃዎን እንዴት እንደምንጠቀምበት እና እንዴት እንደምናሳውቅ፦

- ሕክምና
- ክፍያ
- የጤና እንክብካቤ ስራዎች
- ስልጠና
- ምርምር
- እርስዎን በማነጋገር
- ገንዘብ ማሰባሰብ
- የጋራ ክንዉኖች
- የጤና መረጃ ልውውጥ (HIE)
- የንግድ ተባባሪዎች
- ሌሎች አጠቃቀሞች እና መግለጫዎች

### ሕክምና

ለእርስዎ እንክብካቤ ለመስጠት ወይም ለማመቻቸት የታካሚ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እና ልናካፍል እንችላለን። ለምሳሌ:

- ሐኪሞችዎ ልዩ ምርመራዎችን፣ ሕክምናዎችን እና መድኃኒቶችን ማዘዝ እንዳለባቸው ለመወሰን የእርስዎን መረጃ ይጠቀማሉ።
- ነርሶች፣ ቴክኒሻኖች ወይም ሌሎች ሰራተኞች ስለ መረጃዎ ማወቅ እና ማውራት ሊያስፈልጋቸው ይችላል። እነሱ ህክምናን ለመስጠት እና ለህክምና የሚሰጡትን ምላሽ ለመለካት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።
- መረጃዎን ከሌሎች በማህበረሰብ ውስጥ ካሉ የእንክብካቤ ሰጪዎችዎ ጋር ልናጋራ እንችላለን።

### ክፍያ

ለጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ ለማግኘት የታካሚ የጤና መረጃዎን እንጠቀምበታለን እንድሁም እናጋራለን። ለምሳሌ፡ የጤና መድን ሽፋን ካልዎት እና እኛ በቀጥታ ኢንሹራንሱን የምናስከፍል ከሆነ ማንነትዎን፣ ምርመራዎን፣ የተቀበሉትን አሰራሮች እና የተጠቀምንባቸውን መረጃዎች በመጨመር እናሳውቃለን።

### የጤና እንክብካቤ ስራዎች

የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን የጊዜ ሰሌዳ ለማዘጋጀት፣ ለማጣራት እና ለማሻሻል የታካሚ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እና ልናካፍል እንችላለን። እርሱዎንም ሆነ ሌሎችን የሚንከባከቡ ሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም ለመለካት ልንጠቀምበትም እንችላለን። ለምሳሌ፡ ተቆጣጣር ሀኪሞች የእንክብካቤ ጥራትን ለመለካት የታካሚ መዝገብዎን ሊመለከቱ ይችላሉ።

### ስልጠና

ሰራተኞችን እና ተማሪዎችን ለማስተማር እና ለማሰልጠን መረጃዎን ልንጠቀም እና ልናካፍል እንችላለን። ለምሳሌ፡ የምያስተምሩ ዶክተሮች ከህክምና ተማሪዎች ጋር የታካሚ የጤና መረጃን ሊመለከቱ ይችላሉ

### ምርምር

መረጃዎን ለምርምር ልንጠቀምበት እና ልናጋራ እንችላለን። የተቋማት ግምገማ ቦርድ (IRB) መረጃን ለምርምር ለመጠቀም ወይም ለመግለጽ እያንዳንዱን ጥያቄ ይመለከታል። IRB ለደህንነት ሲባል ፕሮጀክቶችን ይመለከታል እንዲሁም በምርምሩ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች መብቶች የተጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

ያለፈቃድዎ የታካሚ የጤና መረጃዎ ለአንዳንድ ምርምር ሊውል ወይም ሊጋራ ይችላል። ለምሳሌ፡ እኛ ማድረግ የምንችለው፦

- የብስክሌት ቆብ የሚለብሱ ሰዎች ያነሱ የጭንቅላት ጉዳቶች የሚደርስባቸው ከሆነ ለማየት የሕክምና ሰንጠረዦችን እንመለከታለን።
- ለካንሰር ምርምር ጥናት በቂ ታካሚዎች እንዳሉን ለመወሰን የታካሚ ጤና መረጃን እንጠቀማለን።
- በምርምር የመረጃ ቋት ውስጥ የታካሚ ጤና መረጃን ማካተት።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ፡ IRB ያለ እርስዎ ፈቃድ መረጃዎን ለመጠቀም ጥሩ ምክንያት ካለን በመጀመሪያ ይወስናል። በተጨማሪም IRB የመረጃዎን አጠቃቀም ለመገደብ እርምጃዎችን መውሰዳችንን ያረጋግጣል። ለምርምር አስፈላጊ ከሆነ IRB ተመራማሪዎች እርስዎን የሚለዩ መረጃዎችን እንዲቀዱ ሊፈቅድላቸው ይችላል።

በሌሎች በሁሉም ጉዳዮች ላይ፡ በምርምር ፕሮጀክት ውስጥ ከመሳተፍዎ በፊት መረጃዎን ለመጠቀም ወይም ለማጋራት የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት ሊኖርብን ይሆናል። እኛ ስለ እርስዎ የታካሚ የጤና መረጃን በሌሎች ተቋማት ለሚገኙ ተመራማሪዎች ለማጋራት ፈቃድዎ ሊያስፈልገን ይችላል ወይም IRB ከፈቀደ ልናጋራ እንችላለን።

## እርስዎን ለማነጋገር

የታካሚ የጤና መረጃዎ እርስዎን ለማነጋገር ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ፡ ለሚቀጥለው ምክንያት ወደ እርስዎ መደወል ወይም ደብዳቤ መላክ እንችላለን፦

- ቀጠሮዎችን በተመለከተ ልናስታውስዎት።
- የምርመራ ውጤቶችን ለማቅረብ።
- ስለ ሕክምና አማራጮች እርስዎን ለማሳወቅ።
- ስለ ጤና ትምህርት ዝግጅቶች ወይም አገልግሎቶች እንዲያውቁ ለማድረግ።

## ገንዘብን ማሰባሰብ

Children's እንደ ስምዎ፣ አድራሻዎ፣ የስልክ ቁጥርዎ፣ እና የአገልግሎትዎ ቀን ለታካሚ የጤና መረጃ ለፋውንዴሽን እና ለጉልድ ማኅበራችን (Foundation and Guild Association) ሊሰጥ ይችላል። ይህ መረጃ ስለ ልጆች የጤና እንክብካቤ ተልዕኮ የሚደረግ የገንዘብ ማሰባሰብ በተመለከተ እርስዎን ለማነጋገር ሊያገለግል ይችላል። የገንዘብ መሰባሰብ በተመለከተ ማንኛውም አላል ከደወለልዎት እንደገና እንዳይደውልልዎት መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄዎን ማክበር አለብን።

## የጋራ ክንዉኖች

አቅራቢዎች ከሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር ለሚያደርጉት የጋራ ክንዉኖች ቀጥሎ ለተዘረዘሩትን ምክንያት የታካሚ የጤና መረጃዎን ሊጠቀሙ ወይም ሊያካፍሉ ይችላሉ፦

- ክሊኒካዊ እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማቅረብ
- ለክሊኒካዊ እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ ማግኘታችንን ለማረጋገጥ
- ሌሎች የጋራ የጤና እንክብካቤ ሥራዎችን ለማከናወን። ለምሳሌ፡ ለጋራ እንቅስቃሴዎች የታካሚ የጤና መረጃዎን ከሐኪም ቡድኖች እና ከ Children's የህክምና ሰራተኞች አካል ከሆኑ ሌሎች ሀኪሞች ጋር ልናጋራ እንችላለን።

## የጤና መረጃ ልውውጥ (HIE)

Children's በጤና መረጃ ልውውጥ (HIE) ውስጥ ይሳተፋል። HIE ሆስፒታሎች፣ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች የጤና መረጃዎን የሚያጋሩበት የኤሌክትሮኒክ አሰራር ሲስተም ነው። የ HIE ተሳታፊዎች ለህክምና፣ ለክፍያ፣ እና ለጤና አጠባበቅ ክዋኔዎች እንደ አስፈላጊነቱ የታካሚ የጤና መረጃዎችዎን ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም ጥራትን ለመለካት እና አገልግሎቶችን ለማሻሻል ከሚፈልጉ ሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር በጋራ ለሚሰሩ ክንዉኖች መረጃዎን ሊደርሱበት ይችላሉ።

የጤና መረጃዎ በቀጥታ ወደ HIE ውስጥ ይካተታል። በ HIE በኩል የጤና መረጃዎን ላለማጋራት ከፈለጉ ይህንን ከሲስተሙ መጋራት አልፈልግም የሚለውን መምረጥ አለብዎት። የበለጠ ለመረዳት Www.seattlechildrens.org/HIE ን ይጎብኙ ወይም በ 1-866-987-2000 በመደወል፤ ኤክስተንሽን 7-4444 ወይም 206-987-4444።

## የንግድ ተባባሪዎች

አንዳንድ አገልግሎቶቻችን የሚሰጡት በንግድ ተባባሪዎች ነው። ስራዎቻቸውን እንዲሰሩ የታካሚ የጤና መረጃዎን ለእነሱ ልናካፍላቸው እንችላለን። አንዳንድ የምንጠቀምባቸው የንግድ ተባባሪዎች ምሳሌ፡ የአስተዳደር አማካሪዎች፣ ኦዲተሮች፣ የጽሑፍ ግልበጣ አገልግሎት ሰጪዎች፣ እና የመረጃ ማከማቻ አገልግሎቶች ናቸው። የመረጃዎን ሚስጢራውነት ለመጠበቅ የንግድ ተባባሪዎቹ ውል እንዲፈርሙ እንጠይቃለን።

## ሌሎች አጠቃቀሞች እና ይፋ መድረግያዎች

የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶቻችን የተሻለ ለማድረግ፣ የታካሚዎቻችን ደህንነት እና የህዝብ ጤናን ለመጠበቅ፣ የመንግስትን እና የእውቅና ማረጋገጫ መስፈርቶችን መከተል እና እንዲሁም በሕግ በሚፈቀድበት ጊዜ የእርስዎን የታካሚ የጤና መረጃ ልናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፡ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት መረጃ ልንሰጥ እንችላለን፦

- ለጤና እንክብካቤ ቁጥጥር ኤጀንሲዎች ለኦዲት ወይም ፈቃድ ለመስጠት
- ለህዝብ ጤና ባለሥልጣናት፡ ስለ ተላላፊ በሽታዎች እና ስለ አስፈላጊ መዝገቦች
- ለመንግስት ኤጀንሲዎች፡ ለበደል ወይም ቸልተኝነት ስንጠረጥር
- ለጤና መድን እና ለጤና አገልግሎት መምሪያ፡ የጤና ኢንሹራንስ የተጠያቂነት ሕግ (HIPAA) መስፈርቶችን የምናከብር መሆናችንን ለማረጋገጥ
- አግባብነት ላላቸው ግለሰቦች፡ ለጤንነት ወይም ለደህንነት ከባድ አደጋን ለማስወገድ ወይም በሌሎች ላይ ከባድ ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል
- በሰውነት ክፍል ልገሳ እንቅስቃሴዎች ላይ የተካኑ ድርጅቶች
- ለሕግ አስከባሪዎች፡ በሕግ ሲጠየቅም ሆነ ሲፈቀድለት
- ፍርድ ቤቶች ሲታዘዙ፣ ወይም ሕጋዊ ጥሪ ሲደረግ
- FDA
- ለሰራተኞች ካሳ ፕሮግራም
- ክሮነር፣ የህክምና መርማሪዎች እና የቀብር አስፈጻሚዎች
- የአሜሪካ እና የውጭ ወታደራዊ ባለሥልጣናት
- እንደ ብሔራዊ ደህንነት ያሉ ለተለዩ የመንግስት ተግባራት የሚያስፈልጉ የመንግስት ባለሥልጣናት እንደአስፈላጊነቱ
- ለአደጋ የእርዳታ ጥረቶች እንዲረዱ በሕግ የተፈቀዱላቸው የመንግሥት ወይም የግል ድርጅቶች (እንደ FEMA ወይም የአሜሪካ ቀይ መስቀል ያሉ)

## የእርስዎ ፈቃድ ሊኖረው የሚያስፈልገው አጠቃቀም እና መግለጫዎች

በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ከተዘረዘሩት አጠቃቀሞች እና መግለጫዎች ውጭ፡ የእርስዎ  የታካሚ የጤና መረጃን ያለ እርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ አንጠቀምም ወይም አናጋራም። የጽሑፍ ፈቃድ ከሰጡን፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ካልሆኑ በስተቀር፡ ያንን ፈቃድ በማንኛውም ጊዜ መሰረዝ ይችላሉ፦

- ቀደም ሲል ለተቀበሏቸው አገልግሎቶች ክፍያ ለማግኘት መረጃውን ይፋ ማውጣት ካስፈለገን።
- እኛ ቀድሞውኑ በተሰጠው ፈቃዱ ላይ መሰረት የሰራን ከሆነ።
- ህጉ እንዳይሰርዙ የሚከለክል ከሆነ።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ህጉ ለአደንዛዥ ዕጽ እና ለአልኮል ህክምና መዛግብት እንዲሁም ለአእምሮ ጤና መዛግብት ለተወሰኑ የሕመምተኛ የጤና መረጃዎች ልዩ የሆነ የጥበቃዎችን ይሰጣል። በሕግ በሚጠየቅበት ጊዜ ያንን መረጃ ለመጠቀም ወይም ለመግለጽ የእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ለማግኘት እናነጋግርዎታለን።

የታካሚ የጤና መረጃዎን ለግብይት ዓላማ ከመጠቀምዎ ወይም ከማሳወቃችን በፊት ወይም ከመሸጣችን በፊት ከእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ሊኖረን ይገባል።

# የታካሚ የጤና መረጃዎን እንዳናጋራ ሊጠይቁን የሚችሉበት ጊዜዎች

## የሆስፒታል ታካሚዎች ማውጫ

ወደ ሆስፒታል ከገቡ ማውጫው ውስጥ ይገባሉ። ይህ መረጃ ስምን፣ በሆስፒታሉ ውስጥ የሚገኙበትን ቦታ፣ እና አጠቃላይ የጤና ሁኔታን ብቻ ያጠቃልላል (ለምሳሌ፡ "ደህና"፣ "ከባድ"፣ "ወሳኝ")። ይህንን ላለመናገር እስካልፈለጉን ድረስ ይህንን መረጃ ለጎብኝዎች ወይም በስማችሁ ለሚጠይቁ ደዋዮች እንሰጣለን። በመግቢያ ቅጽ ላይ ስለ ቤተሰብዎ ሀይማኖት ለመጻፍ መምረጥ ይችላሉ። ይህን ካደረጉ፡ ስምዎን እና የሆስፒታል አድራሻዎን ለሀይማትዎ ቄሶች ልንሰጥ እንችላለን።

የታካሚ የጤና መረጃዎን እንዳናጋራ ሊጠይቁን የሚችሉበት ጊዜዎች፦

- የሆስፒታል ታካሚ ማውጫ
- ለቤተሰብ፣ ለጓደኞች፣ ወይም ለሌሎች ይፋ ማድረግ

## ለቤተሰብ፣ ለጓደኞች፣ ወይም ለሌሎች መረጃ ይፋ ማድረግ

ይህንን ላለመናገር እስካልፈለጉን ድረስ የእርስዎ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ሰጪዎች ሙያዊ ብቃታቸውን በመጠቀም ለቤተሰብ አባልዎ፣ ለጓደኛዎ፣ ወይም ስምዎ ለሚጠሩት ሌላ ሰው ተገቢውን የታካሚ የጤና መረጃ ይሰጡታል።

# በዚህ ማስታወቂያ የተሸፈኑ ሌሎች አቅራቢዎች

## Seattle Cancer Care Alliance (SCCA)

SCCA ከ Children's፣ ከ UW ሜዲካል፣ እና ከፍሬድ ሁቺንሰን የካንሰር ምርምር ማዕከል ጋር በመሆን ለአንድ ጊዜ ታካሚ እና ለተመላላሽ ታካሚ እንክብካቤን ይሰጣል። ለህክምና፣ ለክፍያ፣ እና ለአንዳንድ የጋራ የጤና አጠባበቅ ክዋኔዎች ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የታካሚው የጤና መረጃ በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ይጋራል። ይህ ማስታወቂያ SCCA በ Children's ላይ ለሚሰጠው የሕክምና መረጃዎን ስለመጠቀም እና ይፋ ማድረጉን ይመለከታል። ለሁሉም የ SCCA ተግባራት የሚመለከተውን የ SCCA የግላዊነት ልምዶች መግለጫ ለማግኘት እባክዎ የግላዊነት ልምዶቹን ማስታወቂያ ይመልከቱ።

## የ UW መድሃኒት እና የ UW የጥርስ ህክምና ትምህርት ቤት (UW SOD)

UW Medicine እና UW SOD በፋኩልቲ ዶክተሮች፣ በጥርስ ሀኪሞች እና በሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች በኩል በ Children's ክሊኒካል እንክብካቤ አገልግሎቶች ይሰጣሉ ወይም ይሳተፋሉ። ለህመም፣ ለክፍያ እና ለአንዳንድ የአገሮች ግምገማ እና የጥራት ማሻሻያ እንቅስቃሴዎች፣ የእውቀና አሰጣጥ ተግባራት እና የሰልጣኞች ግምገማ ያሉ ተገቢ የህመምተኞች የጤና መረጃ ከ Children's እና ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር ይጋራል።

## የልጆች ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ቡድን (CUMG)

የዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ቤት ፋኩልቲ ሐኪሞች ለትርፍ ያልተቋቋመ የጤና አጠባበቅ አቅራቢ ከ CUMG ጋር በመተባበር በ Children's ክሊኒክ እንክብካቤ አገልግሎት ይሰጣሉ ወይም ይሳተፋሉ። ለህመም፣ ለክፍያ እና ለአንዳንድ የጋራ የጤና እንክብካቤ ስራዎች ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የታካሚ የጤና መረጃ በ Children's እና በ CUMG መካከል ይጋራል። ምሳሌዎች፡ የጥራት ምዘና እና የማሻሻል እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ፤ የጤና እንክብካቤ ባለሙያዎችን ብቃት ወይም የቁጥር ጥቅሶችን መመርመር፤ ተገዢነት ያላቸው መርሃግብሮችን ማዘጋጀት፤ እና በንግድ እቅድ፣ ልማት እና አስተዳደር እና በአጠቃላይ አስተዳደራዊ ተግባራት ላይ መሰማራትን ያጠቃልላሉ።

## አድልዎ ከህግ ጋር ይቃረናል

Seattle Children's ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌዴራል እና ሌሎች የሲቪል መብቶች ሕጎችን የሚያከብር መሆኑ ሰዎችን በዘር፣ በቀለም፣ በሀይማኖት (በእምነት)፣ በጾታ፣ በጾታ ማንነት ወይም አገላለጽ፣ በጾታ ዝንባሌ፣ በብሔረሰብ (የዘር ግንድ)፣ በዕድሜ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ ወይም ሌላ በክልል ወይም በአካባቢ ሕግ የተጠበቀ ማናቸውም የሁኔታ ደረጃ መሰረት በማድረግ በሰዎች ላይ የአድልዎ፣ የማግለል ድርጊት አያደርግም ወይም በተለየ አይን አያያቸውም።

## ለአካል ጉዳተኞች ነጻ እርዳታዎች እና አገልግሎቶች

የአካል ጉዳተኛነት ላላቸው ሰዎች፡ እንደ ታካሚዎች እና እንክብካቤ ሰጪዎች፡ ከእኛ ጋር ውጤታማ በሆነ መንገድ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ለማገዝ Seattle Children's ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የነጻ እርዳታዎች እና አገልግሎቶች ይሰጣል፦

- ብቃት ያላቸው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች
- በሌላ ቅርጽ የቀረቡ የመረጃ ጽሑፎች (ለምሳሌ፡ በትልቅ የታተሙ፣ ኦዲዮ፣ ተደራሽ ያላቸው ኤሌክትሮኒክ ቅርጸቶች)

## ነጻ የቋንቋ አገልግሎቶች

Seattle Children's እነዚህን ነጻ የቋንቋ አገልግሎቶች እንደ ታካሚዎች እና ተንከባካቢዎች የመሳሰሉት የመጀመሪያ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ያልሆነ ሰዎችን ይሰጣል።

- ብቃት ያላቸው አስተርጓሚዎች
- በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፈ መረጃ

እነዚህን አገልግሎቶች ከፈለጉ እርዳታ ለሚሰጥዎ ሰው እርዳታ እንደሚፈልጉ ይንገሩ ወይም በ 206-987-2201 በመደወል የቤተሰብ የመረጃ ምንጭ ማዕከልን ያነጋግሩ።

## ቅሬታዎች?

**Seattle Children's የታካሚ እና የቤተሰብ ግንኙነቶች**

Seattle Children's እነዚህን አገልግሎቶች መስጠት አለመቻሉን ወይም በምንም ዓይነት መንገድ አድልዎ አድርገዋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፡ መደበኛ ቅሬታ (አቤቱታ) ለታካሚ እና ለቤተሰብ ግንኙነቶች ክፍል ማቅረብ ይችላሉ፦

- ስልክ/አስተርጓሚ 206-987-2550 ወይም 1-866-987-2000 (ነጻ የስልክ መስመር)። ለአስተርጓሚ 1-866-583-1527 ይደውሉ እና አስተርጓሚውን ከ 206-987-2550 ጋር እንዲያገናኝዎት ይጠይቁ።
- በኦንላይን፡ www.seattlechildrens.org/familyfeedback
- በኢሜይል፡ family.feedback@seattlechildrens.org
- በፖስታ፡ Seattle Children's Hospital
  M/S RB.7.420
  PO Box 5371
  Seattle, WA 98145-5005

  መደበኛ ቅሬታ (አቤቱታ) ለማስገባት እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ፡ ከላይ ያለውን የታካሚ እና የቤተሰብ ግንኙነት ቁጥር ይደውሉ እና አንድ ሰው ይረዳዎታል።

**ወይም**

**የአሜሪካ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፡ ለሲቪል መብቶች ቢሮ**

እንዲሁም ለሲቪል መብቶች ቢሮ ለአሜሪካ የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ፡ የሲቪል መብቶች አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፦

- በኦንላይን፡https://ocrportal.hhs.gov/ocr/portal/lobby.jsf
- ስልክ በመደወል፡ 1-800-368-1019 | 1-800-537-7697 (TDD)
- ደብዳቤ በመጻፍ፡ (Complaint forms are available at www.hhs.gov/ocr/office/file/index.html):
  Centralized Case Management Operations
  U.S. Department of Health and Human Services
  200 Independence Avenue SW
  Room 509F HHH Bldg.
  Washington, D.C. 20201

**If you do not speak English, or if you are Deaf, hard of hearing or Deaf/blind, we will provide interpretation services for you at no charge. Tell the person helping you that you need an interpreter or call the Family Resource Center at 206-987-2201.**

አማርኛ
Amharic

እርስዎ እንግሊዝኛ ባይናገሩ ፣ ወይም መስማት ወይም ማየት የሚሳንዎት ከሆነ ለርስዎ ያለ ምንም ወጪ የአስተርጓሚነት አገልግሎት እንሰጣለን። አስተርጓሚ እንደምፈልጉ ለሚረዳዎት ሰው ይንገሩት ወይም ወደ ቤተሰብ አገልግሎት ማዕከል (Family Resource Center) በ206-987-2201 ይደውሉ።

ترجمه الـ عربـ ية
Arabic

إذا كنت لا تتكلم الإنكليزية، أو كنت أصم، لديك صعوبة في السمع أو أصم/ ضرير، فإننا سوف نقدم لك خدمات الترجمة بدون مقابل. أخبر الشخص الذي يساعدك بأنك بحاجة الى مترجم أو اتصل بمركز موارد العائلة على الرقم 206-987-2201 .

ភាសាខ្មែរ ៖
Cambodian

ប្រសិនបើអ្នកមិនអាចនិយាយភាសាអង់គ្លេសបាន ឬអ្នកស្តាប់មិនឮ ឬពិបាកស្តាប់ឮ/ពិបាកមើលឃើញនោះ យើង នឹងផ្តល់សេវាបកប្រែនិយាយផ្ទាល់មាត់ដល់អ្នកដោយឥតគិតថ្លៃបាន ។ សូមប្រាប់អ្នកដែលជួយអ្នកថា អ្នកត្រូវការ អ្នកបកប្រែផ្ទាល់មាត់ ឬក៏ទូរស័ព្ទទៅមណ្ឌលធនធានគ្រួសារ (Family Resource Center)ក៏បាន តាមលេខ ទូរស័ព្ទ 206-987-2201។

简体中文
Cantonese

如果您不说英语，或您患有耳聋、听力障碍或耳聋/眼盲，我们会为您提供免费翻译服务。请告诉接待人员您需要翻译，或致电家庭资源中心206-987-2201。

فارسی
Farsi

**اگر به زبان انگلیسی صحبت نمی کنید، یا ناشنوا، دارای ضعف شنوائی یا ناشنوا/نابینا هستید، ما بطور رایگان خدمات ترجمه شفاهی در اختیار شما قرار خواهیم داد. به شخصی که کمک تان می کند بگوئید نیاز به مترجم شفاهی دارید یا با مرکز منابع خانواده (Family Resource Center) به شماره 206-987-2201 تماس حاصل فرمائید.**

Français
French

Si vous ne parlez pas anglais, ou que vous êtes sourd, malentendant, ou sourd-aveugle, nous vous proposons des services d'interprétation à titre gratuit. Demandez un interprète au personnel ou appelez le Centre de Ressources Familiales au 206-987-2201.

Deutsch
German

Falls Sie kein Englisch sprechen oder falls Sie taub bzw. schwerhörig oder blind bzw. sehbehindert sind, stellen wir Ihnen kostenlos einen Dolmetscher zur Verfügung. Geben Sie uns bitte Bescheid, falls Sie einen Dolmetscher brauchen, oder rufen Sie das Family Resource Center unter der Rufnummer 206-987-2201 an.

हिंदी
Hindi

**यदि आप अंग्रेजी नहीं बोलते हैं, या यदि आप सुन नहीं सकते हैं, आपको ऊँचा सुनाई देता है या आप सुन/देख नहीं सकते हैं, तो हम किसी शुल्क के बिना आपको दुभाषिया सेवाएं प्रदान करेंगे। आपकी मदद कर रहे व्यक्ति को बताएं कि आपको किसी दुभाषिए की ज़रूरत है या फैमिली रिसोर्स सेंटर को 206-987-2201 पर कॉल करें।**

日本語
Japanese

日本語ができない方、耳や目が不自由な方に、無料で通訳サービスを提供いたします。担当者に通訳が必要だと伝えるか、ファミリー・リソース・センター（206-987-2201）までお電話ください。

한국어
Korean

**귀하가 영어를 못하는 경우, 또는 귀하가 청각 장애가 있거나, 난청이거나, 또는 청각/시각 장애가 있는 경우, 저희는 귀하에게 통역 서비스를 무료로 제공합니다. 귀하를 도와주는 도우미에게 통역자가 필요하다고 말씀하시거나, 또는 206-987-2201번으로 가족 상담 센터(Family Resource Center)에 전화하십시오.**

**ພາສາລາວ**
**Lao**

ຖ້າວ່າທ່ານບໍ່ເວົ້າພາສາອັງກິດ, ຫຼືຖ້າວ່າທ່ານຫູໜວກ, ໄດ້ຍິນຍາກ ຫຼື ຫູໜວກ/ຕາບອດ, ພວກເຮົາຈະໃຫ້ ບໍລິການທາງດ້ານການແປພາສາໂດຍບໍ່ຄິດລາຄາ. ຈົ່ງບອກບຸກຄົນທີ່ຊ່ວຍທ່ານວ່າທ່ານຕ້ອງການນາຍແປພາສາ ຫຼື ໂທລະສັບຫາສູນກາງບໍລິການຄອບຄົວທີ່ 206-987-2201.

**简体中文**
**Mandarin**

如果您不说英语，或您患有耳聋、听力障碍或耳聋/眼盲，我们会为您提供免费翻译服务。请告诉接待人员您需要翻译，或致电家庭资源中心 206-987-2201。

**Oromo**
**Oromo**

Yoo afan Ingiliffaa dubbachuu baatte, ykn yoo duudaa taate, dhagayuun sitti ulfaate ykn duudaa/jaamaa taate, tajaajila turjumaanaa kafaltii malee siif dhiyeesina. Nama isin gargaaru ti akka turjumaana barbaadan itti himaa ykn Gidugaleessa Gargarsa Maatii 206-987-2201 dhan bilbilaa.

**ਪੰਜਾਬੀ**
**Punjabi**

**ਜੇ ਤੁਸੀਂ ਅੰਗ੍ਰੇਜ਼ੀ ਨਹੀਂ ਬੋਲਦੇ ਹੋ, ਜਾਂ ਜੇ ਤੁਸੀਂ ਸੁਣ ਨਹੀਂ ਸਕਦੇ ਹੋ, ਤੁਹਾਨੂੰ ਉੱਚਾ ਸੁਣਾਈ ਦਿੰਦਾ ਹੈ ਜਾਂ ਤੁਸੀਂ ਸੁਣ/ਦੇਖ ਨਹੀਂ ਸਕਦੇ ਹੋ, ਤਾਂ ਅਸੀਂ ਕਿਸੇ ਮੁੱਲ ਦੇ ਬਿਨਾਂ ਤੁਹਾਨੂੰ ਦੁਭਾਸ਼ੀਆ ਸੇਵਾਵਾਂ ਮੁਹੱਈਆ ਕਰਾਂਗੇ। ਤੁਹਾਡੀ ਮਦਦ ਕਰ ਰਹੇ ਵਿਅਕਤੀ ਨੂੰ ਦੱਸੋ ਕਿ ਤੁਹਾਨੂੰ ਕਿਸੇ ਦੁਭਾਸ਼ੀਏ ਦੀ ਲੋੜ ਹੈ ਜਾਂ ਫੈਮਿਲੀ ਰਿਸੋਰਸ ਸੈਂਟਰ ਨੂੰ 206-987-2201 'ਤੇ ਕਾਲ ਕਰੋ।**

**Română**
**Romanian**

Dacă nu vorbiţi limba engleză sau dacă sunteţi surd(ă), aveţi probleme cu auzul sau sunteţi surd(ă) şi orb(oarbă), vă vom oferi servicii gratuite de interpretariat. Spuneţi-i persoanei care vă ajută că aveţi nevoie de un interpret sau sunaţi la Family Resource Center (Centrul de resurse pentru familii) la 206-987-2201.

**Русский**
**Russian**

Если Вы не говорите по-английски или если Вы глухие, слабослышащие или глухие/слепые, мы предоставим Вам бесплатные переводческие услуги. Скажите помогающему Вам лицу, что Вы нуждаетесь в переводчике или позвоните в Центр помощи для семьи по тел. 206-987-2201.

**Af-soomaali**
**Somali**

Haddii aadan ku hadlin ingiriisiga, ama haddii aad dhagoole tahay, maqalku kugo adag yahay, ama dhagoole/indhoole tahay, waxaad heli kartaa in laguu turjumaano adiga oon wax lacag ah bixiin. U sheeg qofka ku caawinaya in aad u baahan tahay turjumaan ama wac 206-987-2201 xarunta khayraadka qoska.

**Español**
**Spanish**

Si no habla inglés o si es sordo, tiene problemas de audición o es ciego y sordo, nosotros le proporcionaremos servicios de interpretación sin costo alguno. Dígale a la persona que le está ayudando que necesita un intérprete o llame al Centro de Recursos para Familias al 206-987-2201.

**Tagalog**
**Tagalog**

Kung kayo ay hindi nagsasalita ng Ingles, o kung kayo ay bingi, nahihirapang makarinig o bingi at bulag, bibigyan namin kayo ng interpreter at hindi kayo sisingilin para sa serbisyong iyon. Sabihin sa taong tumutulong sa inyo na kailangan ninyo ng interpreter o tawagan ang Family Resource Center sa 206-987-2201.

**Український**
**Ukrainian**

Якшо Вы не говорите по-англійски, або глухи, с поганим слухом, або глухи/сліпи, ми будемо надавати послуги усного перекладу для Вас безкоштовно. Скажить людині, допомогаючей Вам, що Вам потрібен перекладач або зателефонуйте до Центра допомоги для сімей по тел. 206-987-2201.

**Tiếng Việt**
**Vietnamese**

Nếu quý vị  không nói được tiếng Anh hoặc nếu quý vị bị điếc, khiếm thính hoặc điếc/ mù, chúng tôi sẽ cung cấp dịch vụ thông dịch cho quý vị miễn phí. Hãy nói cho người đang giúp quý vị hay rằng quý vị cần một thông dịch viên hoặc gọi Trung Tâm Nguồn Hỗ Trợ Gia Đình theo số 206-987-2201.

## የግላዊነት መብቶችዎን ለመጠቀም ወይም ቅሬታ ለማቅረብ የሚከተሉትን ማነጋገር ይችላሉ፦

**Children's Privacy Office**
Mailstop RC-402
PO Box 5371
Seattle, WA 98145-5005

206-987-1200
1-866-987-2000, ኤክስተንሽን፡ 7-1200 (ነጻ የስልክ መስመር)
privacy.questions@seattlechildrens.org

## እንዲሁም ቅሬታ ካለዎት የሚከተለውን ማነጋገር ይችላሉ፦

**Office for Civil Rights, Region X**
U.S. Department of Health and Human Services
Mailstop RX-11
2201 Sixth Avenue
Seattle, WA 98121-1831

206-615-2290
206-615-2296 (TTY)
206-615-2297 (Fax)
1-800-362-1710 (Toll-free)
1-800-537-7697 (TTY)

### ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

- በሆስፒታሉ ውስጥ የልጅዎን ነርስ ይጠይቁ።
- ከሆስፒታሉ ውጭ በነጻ የቤተሰብ አስተርጓሚ መስመርን ይደውሉ 1-866-583-1527። የሚፈልጉትን ስም ወይም ቅጥያ ለአስተርጓሚ ይንገሩ።

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

4800 Sand Point Way NE
PO Box 5371
Seattle, WA 98145-5005

206-987-2000
1-866-987-2000 (ለንግድ ስራ ብቻ፡ ነጻ የስልክ መስመር)

1-866-583-1527 (የቤተሰብ የትርጓሚ መስመር)
www.seattlechildrens.org

በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ የግላዊነት ልምዶችን የመቀየር መብታችን እና አሁን ላለው እና ለወደፊቱ የታካሚ የጤና መረጃዎ እነዚህን ለውጦች የማድረግ መብት አለን። የአሁኑ ማስታወቂያ በ Children's ተቋማት ላይ እንለጥፋለን። አንድ ቅጂ ከማንኛውም የ Children's ተቋም፣ በሆስፒታሉ ከሚገኘው የቤተሰብ የመረጃ ምንጭ ማዕከል ወይም በ www.seattlechildrens.org በኩል መጠየቅ ይችላሉ።

Children's በተጠየቀ ጊዜ ይህንን መረጃ በአማራጭ ቅርጸቶች ያቀርባል። በስልክ ቁጥር 206-987-2201 የቤተሰብ የመረጃ ምንጭ ማዕከልን ይደውሉ።

© 2018 Seattle Children's, Seattle, Washington. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

1/18
PI397AM